# ሩቅ ሀገር ያስዋሻል፤ መጥፎ ሰው ያንቋሽሻል

## (ርሑቅ ዓዲ መሐሰዊ፤ ሕማቅ ሰብ መናሸዊ)

ከመላኩ ይስማው

“መርሳትን ነው መርሳት!” በሚል ርዕስ ታላቁ የቅኔ ሰው ሃይሉ (ገሞራው)፡

ሙጥኝ አሻፈረን — እያሉ ተማጥነው፣
ጥቃቅን ግዙፉን — እንደያይነታቸው፣
በዚህ ዓለም አሉ — ኗሪ ሐቅን መስለው።
ፈረንጅ እንደሚለው — At closest range
ቀርበን ብናያቸው — በርግጥ አወናባጅ፣
ናቸው በባሕርይ — የሀሰት ጉርማጅ።

........................................................

ማስመሰል ማስረሳት — ሁለቱ አንድ ናቸው፣
ጭብጡን ለመደበቅ — ነውና ግባቸው።
ማስመሰልን ትተን — ማስረሳትን ብናይ፣
ሰለባ ያደርጋል - በሰባኪ አታላይ!
ማስረጃ ልደርድር — ባንዳንዶቹ ጉዳይ።

እያለ ድንቅ ግጥሙን "ቆርጠሀት ጣልልኝ?” በሚለው መድብሉ ውስጥ ያሳተመው በ1992 ዓ. ም. ነው። ባንዳ በነበረ የንጉሡ ሹመኛ ፍርድ ለአርበኝነቱ ዋጋ በአንገቱ ገመድ የገባለት በላይ ዘለቀም ምሬቱ ቢበዛበት "ወንድ ልጅ አይብቀልብሽ!” አለ የሚል አባባል አለ። በቃላዊ ሥነጽሁፋችንም ውስጥ "ኢትዮጵያ ሀገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ፣ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ!” የሚል ሌላ አባባል ይገኛል። አሁን አሁን ግን ነገረ ስራችንን ልብ ላለ፣

ኢትዮጵያ ሀገሬ፣ ሞኝነትሽ በዛ፣
ካንች በፊት ባለው፣ በሞተልሽ ፈንታ፣
የገዳይሽ  ፍቅር፣ በግልብጥ ተነዛ።

ያሰኛል። ያልታደለች ሀገር ቢባል ምናልባት የተሻለ ሊሆን ይችላል።

- ለሀገር ቅርስ የሆኑ ሳይከበሩ ቀርተው አልፎም ሲረሱ ሲነጠሉ፤
- ወንጀለኛ ነፍሰገዳዮችና ጭራቆች ሲወደሱና ሲከበሩ፣
- አፍራሾችና አንጃዎች ህብረት ሲያቀነቅኑ፣
- ነፍሰ ገዳዮችና ፈርጣጮች አዲስ ታሪክ ሲጠርቁ፣
- የምሁር ሚዛን ቀንሶ ጥራዝ ነጠቆች መድረኩን ሲያጨናንቁ፣
- ዜጎች በወያኔ ላይ ማዕቀብን ሲዘነጉ፣

መታዘብ የዘወትር ክስተት እየሆነ ነው።  ብዙ ምሣሌ መጥቀሱን መቀጠል ይቻላል። ግን ነገር ቢበዛ  በአህያ አይጫንም ቢሆንም፣ ከዛሬ ያስቸገረን ጅብ አያሳድረንም ነውና የዘነጉን ማስታወስ፤ የሚያንቀላፉትን ለመቀስቀስ መሞከሩ አይከፋም።

ተቋሙ ሲድ ብለውታል - በዚያው በሚወዱት ፈረንጂኛ ቋንቋ — እንግሊዝኛ። አነሳሱ ቀና ነበር — በጎ ሰሪዎችን ለማበረታታት፤ አርአያነታቸውን ለማድነቅ። ያመንኩት ፈረሴ ገዳዬ ሆነ ተብሏልና እያደር ሲድ በብዙ ፈርጅና ግምገማ ከሕዝብ ጎራ የማይመደቡትን ለምሳሌ ዶክተር ፀሐይ የተባለውን የትግራይ ትምክህተኛ ዓይነቶቹን ሁሉ መሸለምን ተያያዙት። የ ሲድ ሚዛን ከባድ ባይሆንም ድርጊታቸው ግን ሀገራችን ወይም የሀገራችን ነቃን ባይ ዜጎች ሆኑ ገዢዎች ምንኛ

መከበር ያለባቸውን ልጆቿን እንደማታከብር ወይም እንደማያከብሩ እንደገና ያሳየናል። አጼ ሀይለስላሴ ግራ ቀኙን፤ በመሀል ከተማ ያለውን መጸዳጃ ሁሉ ሳይቀር በስማቸው አስጠሩ ተብሎ ሲተቹ ነበር። አርበኞችና ሌሎችም ይቅሩና እነ አበበ ቢቂላ ሁሉ ተረስተው ነበር። የአፄ ቴዎድሮስ ታሪክም በአሉታዊ መፃፉ ምሳሌ ነው። ሜሪ አርምዴ ረጂ አጥታ ሞተች። ቆይቶም ብዙነሽ። በዘመነ ደርግ የሁሉም በላይና አልፋ ኦሜጋ ነፍሰ ገዳይ ኮለኔል ነበር። የሀገር ቅርሶች ለእስር ተዳረጉ ወይ ተገደሉ። ስንት የሀገር ምስጢር የሚያውቁ ሚኒስቴሮች በግፍ ተረሸኑ። ስንቱ ሀገር ገንቢ ወጣት ተጨፈጨፈ። የሀገሪቷ ጋዜጦችና መገናኛ ብዙሃን ብቻ ሳይሆኑ ምሁር የተባሉትም ጭምር ክቡር ሊቀ መንበር ብለው ሲሰግዱለት እንደነበርም ይታወሳል። ዛሬም ከነዚህ አንዳንዶቹ የገለማ አቋማቸውን ይዘው የወንጀል ደጋፊና የወንጀለኛ አዳናቂ መሆናቸውን ደግሞ ወደታች እጠቅሳለሁ። ወያኔ ግን ወያኔ ነውና ኢትዮጵያን የሚያስከብሩትን ቢንቅ፤ እነ ይድነቃቸው ተሰማን ቢያክቾለችል፤ እነ ሎሬትን ቢያሳድድ፤ እነ ሀይሉ ገሞራውን በተሰደዱብት ቢያሳድድ፤ ውድ ዜጋዎች በሀገራቸው እንዳይቀበሩ ቢያግድ፤ እርቅ ያሉትን ቢቀፈድድ፤ ወንጀለኞችን ቢያቅፍ አስገራሚ ጉዳይ አይሆንም። እነ ሎሬትም በስደት አረፉ፤ እነ ጸጋዬም (ደብተራው) ደብዛቸው ጠፋ፤ እነ ገሞራውም ባሉብት ተጠበሱ ። ወያኔ ወያኔ ነው። ጸረ-ኢትዮጵያ ነው። የነ ሲድስ ምን ይባላል? የወያኔ ዶክተርን ከመሸለም፣ ታዋቂውን የሀገር ቅርስና የኪነት ሰው ገሞራውን መሸለም የተሻለ አይሆንም ነበር? የሀገርን ስም የሚያስጠሩ ሀገር ወዳድ ቅርሶችስ በፖለቲካ አቋማቸው ብቻ ከእኛ አልገጠሙም በሚል መፈጠራቸውንም እስከመካድና መርሳት መድረሱ ምን ይባላል? የመጥፎ ዘመን ባለጊዜዎችን ማዳነቁስ መቼ ያከትማል?

ይባስ ብሎ ደግሞ ወንጀለኛና ጭራቅ ነፍሰ ገዳዮችን ማዳነቅና ማወደስም ገኗል። በቅርቡ የወንጀለኛው ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ መጽሐፍ ዕጹብ ድንቅ ተብሎ በአንድ ድረ ገጽ ሲነበብ ነበር። ለአረመኔው ተስፋዬ ወልደ ስላሴም አላማረብህም የሚለው ያጣ አንድ የዘመኑ "ጋዜጠኛም" ሲያላዝንለት ተደምጧል። ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ በወያኔ ትዕዛዝ በጻፈው ቡትቶ ኢሕአፓን አውግዞና ታሪክ አጣሞ ለማቅረብ ጥሯል። ሌላው ቀርቶ የደርግ ጊዜ ወዳጆቹንም ክዷል። ቁመነገሩ ግን በደርግ ዘመን ዋና ስራው (ዛሬ በባልቲሞር ኣሜሪካ ከሚኖረው ኢሳያስ ሀብተ ማርያምና ከህግ ትምህርት ቤት ምሩቅ ከነበረው ሰይፉ ጋር ሆኖ) የእስረኞችን ጉዳይ አጥንቶ <u>ይገደል አይገደል</u> ለውሳኔ ማቅረብና በዚህም መልክ ብዙዎችን ማስገደል ነበር። በነፃ ኢትዮጵያ ተስፋዬ ርስቴና መሰሎቹ ለሕዝብ ፍርድ የሚቀርቡ ሆኖ ሳለ በባዕድ ሀገር ሆነው እነዚህን ጭራቆች የሚያዳንቁ ምን ሊባሉ ይሆን? ወንጀለኞችን እያዳነቁና እያወደሱ በዚያው አፋቸው ደግሞ የህዝብ ወገን ብቻ ሳይሆን የተጋይም ታጋይ ነን የሚሉ ከንቱዎች በአሁኑ ጊዜ የሕዝብን ትግል እየጎዱ መሆናቸውን አውቆ በጥብቅ ማውገዝና ከሕዝብ ጎራም መንጥቆ አውጥቶ ወደ ታሪክ ትቢያ መጣል ግዳጃችን መሆን አለበት።

ከነዚህ የታሪክ አተላዎች አንዳንዶቹ ደግሞ በቅጥረኛነት ሆነም አልሆነ ሕዝብ በጠራራ ፀሐይ የሚያውቀው ሚናቸው የአፍራሽነት ሆኖ ሳለ ከመፍጥነት የህብረት አባወራ ነን ብለው የባለጌ ሰርግን ይሰብካሉ። በአንድ ጎን የነበሩበትን ድርጅት ለወያኔ እጅ መንሻ ሊያቀርቡ ሞክረው፣ አልሳካ ሲላቸው በሌላ በኩል በአንድነት ወያኔን ስለመታገል

ይሰብካሉ። በአንድ “የኮሚቴ ቱሪስቶች እና ታርጋቸው” በሚል ርዕስ ባቀረብኩት መጣጥፍ ያነሳሳሁዋቸው “ድርጅት ያለሽ ለዋሎች” ደግሞ አሉ። አንዱን የነበረበትን በኢትዮጵያ አንድነት አማኝ ድርጅት ለማፈራረስ ሲሞክር የዕብድ ገላጋይ ሆነው፣ ዋና አስተናጋጅ ሆነው ግፋ በለው እንዳላሉ፣ ዛሬ ደግሞ አዛኝ ቅቤ አንጓች፣ የውሽማ ሽማግሌ ካልሆን የሚሉ። በኢትዮጵያዊነቴ ላይ ሕዝበ-ውሳኔ ካልተደረገ ከሚሉት እንገንጠል ባዮች ጋር ታንጎ እየደነሱ፣ ስለኢትዮጵያ የሚሰብኩን። ጥንቸል ከኔ በላይ የሚዘሉ ያበዱ ያለችውን ያስታውሷል። እውን ህብረትን ከልባቸው ከፈለጉ ለምንስ ድርጅታቸውን ለማፍረስ ተነሱ፤ ቃጡ፡ ተቅበዘበዙ ብሎ መጠየቅ አግባብ ያለው ይሆናል። እነዚህን አወናባጆች ሀገር ወዳድ ሁሉ ወግዱ ሊላቸው ይገባል። በርግጥ ከዓይናችን ራቁ ብሎ እያሳፈራቸውም ነው።

ህብረትን በተመለከተ ግን አሁንም የተሳሳቱ ግንዛቤዎች ሰፍነው ይታያሉ። አንደኛው ለኢትዮጵያ በሚበጅ መንገድ በኢትዮጵያዊነት አምነው ሊተባበሩ የማይፈልጉትንና አንፈልግም ያሉትን ለማቀፍ የሚደረገው ከንቱ ልፋትን ይመለከታል። ሁለተኛው ደግሞ ምትሐት የወረቀት ቡድኖችን ወይም አባልም እንቅስቃሴም የሌላቸውን አቅሮ ከእጅ አይሻል ዶማን ፖለቲካ ያውም በባዕድ ሀገር እያካሄዱ ጊዜና ጉልበትን በማጥፋት አጓጉል መዳከር ነው። ህብረት የህልው ድርጅቶች ኢትዮጵያዊ ጥረትና ፍላጎት ውጤት እንጂ የአፋራሽና አንጃ ጥርቅሞች፤ ኢትዮጵያዊነትን የካዱና አንቀብልም ያሉ ቡድኖች መሰባሰቢያ ወይም መሳሪያ ሊሆን አይገባውም፣ አይጠበቅምም — ለኢትዮጵያ አንድነት ተሟጋች ወገን።

ከሁሉም የሚብሰው አሳዛኝ ጉዳይ ደግሞ ነፍስ ገዳዮች ተመልሰው ሰለባቸውን ለማውገዝ፣ በአካል የገደሉትን/ኋትን የሕዝብ ልጅ ታሪክ ለመግደል ታሪክ ፀሐፊ ሲሆኑ፣ ከሀዲና ፈርጣጮችም ያን የውርደት ታሪካቸውን ለመሸፈን ሲሞነጫጭሩ መታዝቡ ነው። ለዚህ ቀደም ብዬ የጠቀስኩት ማፈሪያ የፖሊስ ሻምበል አንድ ምሳሌ ነው። ሌሎችም በየፊናችው ለመሰል ውግዘት በምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉ አሉ። በታሪክ እንደታየው ማተብ በጥሰው፣ ትላንት እንሞትለታለን ያሉለትን መርህ፣ አቋም እና ሕዝብ ክደው በፀረ ህዝብነት የተሰለፉ/የሚሰለፉ ጥቂቶች አይደሉም። ከእነዚህ አንዳንዶቹ አፍረው ዝምታን ሲመርጡ ሌሎች ግን መድረኩን ይዘው፣ አጠፋንን ከምላሳቸው ሳያቀርቡ ያለፈውን ትውልድና ትግል አምርረው የሚያውግዙ አሉ። በደርግ ዘመን በዩኒቨርስቲ የፍልስፍና ትምህርት ክፍል ሀላፊ የነበረው፣ ያን አፀያፊ ስማያዊ ዩኒፎርም ለብሶና ሽጉጥ ታጥቆ ይቧርቅ የነበረው ዶክተር-ፕሮፌሰር ዛሬ እየፃፈ ያለው በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው። በደርግ ባንዳ ምሁርነት ተሰልፎ ሲያገለግል የቆየና የታጋይ ወጣትንም ዓይን በሳንጃ ሊያጠፋ ሞክሮ የነበር ሌላ ምሁርም ያን ትውልድ በጽሁፍ ሲያጠቃ በተደጋጋሚ ታዝበናል። ከሁሉም የምንታዘበው ዋና ቁምነገር ግን በኢሕአፓ ላይ ዘመቻቸው ማተኮሩን ነው። የድርጅቱን ታሪክ ጭራሽም የማያውቁት ነበርን ብለው በቅርቡ በአዲስ አበባ መጽሐፍት ተብዬዎችን አስራጭተዋል። የደም ዘመን፤ የሰራዊት ታሪክ፡ የነዚሁ ግምገማ በሚል ግርግሩ ደራልን ብለው ራሳቸውን ያጋለጡ ብዙ ናቸው። ታሪክ ሊተርኩ አስበውና ተቆርቁረው ሳይሆን ታሪክን ሊበርዙና ሊክልሱ። የተወሰነ ድርጅትን የጎዱ መስሏቸው የሀገርና ህዝብን ታሪክ የሚያቆሽሹትን የሚያቅፉ ያሳዝናሉ ብንል ማጋነን አይሆንም። አሉባልታና መሰረት ቢስን ግምገማ ለቃቅሞ

የኢ.ሕአሰ ታሪክ ብሎ ያቀረበውን የወያኔ ቅቤ ጠባሽ ግለሰብ ጽሁፍ ገመገምኩ ብሎ ሰሞኑን 14 ገጽ ጽሁፍ ያቀረበው የሰሜን ፕሮፌሰር ከእነኝህ አንዱ ነው። ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ከዚህ በፊትም ወያኔን ደግፎ አጥቅቶት የነበረውን ኢ.ሕአፓን ይዘልፋል። ፕሮፌሰሩ ወጣት ሳለ በኢ.ሕአሰ ሀይል 27 የተባለቺውን መሪ ሆኖ ለትዝብትና ለክስም በዳረገው ፍርሓትና ፍርጠጣ የጓዶቹን ሕይወት ማስጠፋቱ የሚታወቅና የማይረሳም መሆኑን ዛሬም የሚመሰክሩ በሕይወት አሉ። ድርጅቱ በራሱ ምክንያት ዝምታን መርጦ ያላጋለጠው ሊሆን ቢችልም፣ ይህን ሀፍረተ ቢስ ግለሰብ በዝምታ ማለፍ ግን ግፍ ነው። ፕሮፌሰሩ ወደ አሜሪካ ካቀናም በሁዋላ የወያኔ ድጋፊ ሆኖ — "ዘር ክልጓም ይስባል" ሆኖበት -- ወያኔም ለስልጣን ሲበቃ፣ ያን አፀያፊ ዘረኛ መጽሔት — ኢትዮጵያን ኮመንቴተር — በዋና አዘጋጅነት ያቀርብ እንደነበር አይረሳም። በ 1995ም መጽሃፍ ጻፍኩ ሲል አሁንም ኢ.ሕአፓን ዘልፎ ወያኔን ማዳነቁ የተመዘገበ ነው። የፍርጠጣና ዘረኛነት ሚናውን ለመደበቅ ሲጥር የሀሰት ታሪክን መጠረቅ ተገዷል። በ ኢ.ሕአሰ ውስጥ ስህተት የተሰራ ቢሆንም ይህ ፕሮፌስር በሉኝ ባይ ዘረኛና ያኛውም ታሪክ ጻፍኩ ባዩ የነበረከት ስምኦን ጓደኛ ሊያቀርቡት እንደፈለጉት ያ የጀግኖች ሰራዊት በአባሎቹ ላይ ግድያና ሰቆቃን የሚፈጽም ከቶም አልነበረም። ስህተቱንም ለማረም የእርምት እንቅስቃሴን ያደረገው በራሱ ነው። ሀቁ ይነገር ከተባለም ኢ.ሕአሰ በልቅ ዴሞክራሲ እንጂ እንደነ ፕሮፌስሩ ጌታ እንደወያኔ በአፋኝነት መቸም አይታማም። <u>ታሪክን በሀሰት የሚተርኩ፣ የሰነቅነውን ብሩህ ነገንም ሊቀሙን የተነሱ መሰሪዎች ናቸውና</u> ነቅተን እናጋልጣቸው።

ይህ ሁሉ የሚጠቁመን ሀገር አኩሪ ምሁሮች ጠፍተው ወይም ድምፃቸው ታፍኖ ጥራዝ ነጠቅ ምሁሮች፤ ባንዳዎችና የወያኔ ዓይነት ዘረኞች ምሁር — ዶክተር ነን ብለው መድረክ ማጠበባቸውን ነው። ያሳዝናል ፤ ያሳስባል። መለስን ጠላን፤ የወያኔን ዘረኛ ስርዓት ግን እናፈቅራለን ባዮች — ከላይ የተጠቀሰው ፈርጣጭ ፕሮፌሰር ዓይነቶቹ — ለሀገር አይበጁም። አፍራሽና ከለልተኛ፤ ዘረኛና አንጃ ቀፍቃፊ ምሁሮችም የሀገር እሬት ናቸው።

በውጭ ሀገርም በወያኔ ላይ ማዕቀቡ ተረስቷል። የአዜብ ጎላ ጤፍ እንጀራ አሁንም እየተሸጠና እየተገዛ ነው። ቢራውም ሌላ ሌላ ቆሳቁሱም። በባዕድ ሀገር ያሉ የወያኔ መደብሮችና ሆቴሎች ንግድ ደርቷል። ምነዋ ሀገር ወዳድ ዜጎች? ማዕቀቡ አይረሳ እንጂ!!

የሀገር አንድነትንና የሕዝብን ዴሞክራሲያዊ መብት ለመታደግ በአለፈውም፣ አሁንም እየተካሄደው ያለው ታሪካችን እና ታጋዮቻችን ላይ ዘመቻው መድራቱ የነገው ሞታችንን፣ የሀገራችንንም ሞት ለማፋጠን የተቀነባበረ ዘመቻ ነው። ሐቅን ለመግደል። እናም ባለቅኔው ቀደም ሲል በጠቀስኩት ግጥሙ ውስጥ እንዳለው፡

ሌላው ሌላው ቢቀር — ያለወንጀላቸው፣
ታርደው የረገፉት — ምን ይለን አፅማቸው፤
እኛን ቋሚዎቹን - እርሱት ከተባለ፣
መርሳትን ነው መርሳት — ሐቅ እስከበደለ!